የሰ/መ/ቁ. 36848

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤ/ኃይል ኮርፖሬሽን

**ተጠሪዎች፡-** 1. መኰንን ግርማይ - ቀረቡ፡፡

2. በዶ ዘለቀ - ቀረበ

3. ፈጠነ አያዩ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የኤሌክትሪክ ምሰሶ ጉድጓድ ለመቆፈር ጊዜያዊ ሠራተኞች በመሆን ሠርተናል፤ በኋላም ወደ ረዳት የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት አሸጋግሮን ስንሰራ ከቆየን በኋላ ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ስላሰናበተን ወደ ስራችን ተመልሰን ቋሚ ሠራተኞች እንድንሆን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎችም በስራ ላይ ደረሰብን ለሚሉት ጉዳት ያወጡት ወጪ ይተካላቸው ዘንድ በተጨማሪ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በእሱ እና በተጠሪዎች መካከል የተደረገ የስራ ውል እንደሌለ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች የአመልካች ሠራተኞች ናቸው፤ የስራ ውላቸው የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው፤ በመሆኑም አመልካች በሕጉ መሠረት የሚከፈሉትን ክፍያዎች እንዲሁም በስራ ላይ ሣሉ ለደረሰባቸው የአካል ጉዳት ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪዎች የአመልካች ሠራተኞች ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የስራ ውልን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው ነው፡፡ ከስር ጀምሮ ከቀረበው የአመልካች ክርክር እንደሚታየው ተጠሪዎች በተባለው የምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ ወይም የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት ስራ አልተሣተፉም አይልም፡፡ ክርክሩ ይህን ስራ የሰሩት ከኔ ጋር የስራ ውል አድርገው ሣይሆን፣ ስራውን እንዲሠራ ኮንትራት ከተሰጠው ግለሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ነው የሚል ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ይህን ጭብጥ በመያዝ ማስረጃ እንደሰማና በዚህም አመልካች ስራውን በኮንትራት የሰጠው ግዛው ወንዳፍራሽ ለተባለ ሰው እንደሆነ፣ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የቅጥር ግንኙነት

እንደሌላቸው፣ ግዛው ወንዳፍራሽ ክፍያውን ሲፈጽም እንደቆየ ማረጋገጡን በአንድ በኩል ሲገልጽ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተከሣሽ /አመልካች/ ከሱ ጋር የቀን ስራ ሲሰሩ አለመቆየታቸውን ሙሉ በሙሉ አልካደም፤ ክፍያው ሲፈፀም የነበረው ከአመልካቹ በተገኘ ገንዘብ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ እንደሰጠ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የተደረገ የሥራ ውል እንደሌለው በግለጽ በማመልከት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎች የተባለውን ስራ ሊሠሩ የቻሉበትን ምክንያትም ከመግለፁም በላይ፣ በቆጠረው ማስረጃም እንደክርክሩ ጭብጥ አስረድቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ሁኔታ በውሣኔዎቻቸው ላይ በሚገባ አስፍረው ግንዛቤ አግኝተው ሣለ ተቃራኒ የሆነውን ውሣኔ መስጠታቸው ትክክል አይደለም፡፡ ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ክርክር ማስረጃ እና በሕጉ መሠረት ብቻ ነው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ቁምነገሮች በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ በማንኛውም መለኪያ ሕጋዊ ሊሆን አይችልም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከቀረበው ክርክር፣ከተሰማው ማስረጃ እና ከሕጉ ውጭ የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06165 መጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05200 መጋቢት 1 ቀን 2000 ያፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የስራ ውል ግንኙነት ስለሌለ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ የመሠረቱት የስራ ክርክርን የሚመለከተው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ